የሰላሑዲን ፍላጎት እና ጥረት በወታደራዊ ምሽጎች ብቻ የታጠረ አልነበረም። ነገር ግን በጂዛ እና በአር-ራዳህ ደሴቶች ውስጥ የተሰያዩ ግንባታዎችን የማከናወን፣ የናይል ወንዝ ጥልቀት የሚለካበትን መለኪያ መሣሪያ ማስቀመጥ እና በርካታ ቦዮችን የመሥራት እቅድ ነበረው፣ በእቅዱ መሠረትም ብዙ ከውኗል። በተጨማሪም ብዙ ሆስፒታሎችን ገንብቷል። ለምሳሌ ያህል ካይሮ ውስጥ የሚገኘውን እና የነፃ እንክብካቤ በመስጠት የሚታወቀውን የማርስታን ሆስፒታል ማንሳት ይቻላል። ሆስፒታሉን የሚቆጣጠር፣ የመድሃኒቶችን ክምችት የሚያስተዳድር በሳም የተማረ ሰው አስተምሮ ነበር። ይህ ሰውዬ መድሃኒቶችን ለበሽተኞች እንዴት በአግባቡ ማድረስ እንዳለበት እና እንዴት በትክክል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ እንደሚችል የተለየ ሥልጠና አሱ ራሱ ሰጥቶት ነበር። እንዲሁም ሆስፒታሉ በሽተኞች ተኝተው የሚታከሙባቸው በርካታ አልጋዎች የነበሩት ሲሆን በተለይ ለሴቶች ብቻ ግልጋሎት የሚሰጡ ክፍሎችም ነበሩት። ከዚህም ሁሉ በላይ በዚሁ ሆስፒታል ውስጥ የአዕምሮ በሽተኞች ብቻ የሚተኙባቸውና መስኮቶቻቸው በፍርግርግ ብረት የተዘጉ ክፍሎች እንዲዘጋጁ አድርጎ ነበር። የአዕምሮ በሽተኞችን የሚንከባከቡ እና ጥያቄዎቻቸውን የሚመልሱ ሠራተኞችን አስተምሮ ነበር።

ኢብን ጁበይር የጉዞ ማስታወሻዎቹን ባሰፈረበት መዕለፉ ጂዛ እና አር-ራዳህ በወቅቱ በአገሪቱ ውስጥ እጅግ የነቃ እንቅስቃሴ ከነበራቸው ዋና ከተማዎች መካከል የሚጠቀሱ ከተማዎች እንደነበሩ ዕሳቤል፦

> ጂዛ ውስጥ አሁድ ቀን በመጣ ቁጥር በየሳምንቱ የሚደምቅ ትልቅ የገበያ ሥፍራ ነበር። እንዲሁም ጂዛን እና ካይሮን በሚለየው ደሴት ውስጥ በሳም ብዙ አይን የሚስቡ ህንፃዎች እና የመዝናኛ ቦታዎች ነበሩ። ከናይል ወንዝ ዳርቻዎች በአንዱ ላይም ጁመዓ የሚሰገድበት ግዙፍ መስጅድ ነበር። ከዚህ መስጅድ ትንሽ ራቅ ብሎ የአባይ ወንዝ መመላለት እና መገደሉን ሰዎች አንብበው የሚያውቁበት የጥልቀት መለኪያ ነበር። የመለኪያ መሣሪያው በከበሩ ድንጋዮች እና በአብነበረድ ያጌጠ ነበር ...

ሰላሑዲን ግብፅን የየበስም ይሁን የባህር ኃይሉ ዋና ማዕከል ድርጎ ይመለከታት ስለነበር መርከቦችን እና ፈጣን ጀልባዎችን ይሠራ ነር። እንዲሁም የባህር ኃይሉን እራሱን ችሎ በአል-ዓዲል የሚመራ ፒፖርትመንት እንዲሆን አድርጎት ነበር። ግብፅ ከውጭው ዓለም ጋ ምትገናኝባቸው ዋና የባህር በሮች አሌክሳንድሪያ እና ዳሚታ ሲሆኑ ባህር የሚመጣን የትኛውንም ዓይነት ጥቃት ለመከላከል ተዘጋጅተው የሚጠብቁ የጦር መርከቦች የሚገኙባቸው ከተማዎች ይግሞ አል-ኦክታት እና ቃስ ነበሩ። የዚህ ሁሉ ጥረቱ ዋና ዓላማ ሌላ ሳይሆን የኢስላም ባንዲራ ከፍ ብሎ ሊውለበለብ ማየት ብቻ ነበር።

ፍራንክች ዓይናቸውን እንደጣሉባት የተገነዘበው ሰላሑዲን ትኩረቱን ወደ አሌክሳንድሪያ በመመለስ ግንቦቿ እና የመቆጣጠሪያ ማማዎቿ እንደገና እንዲገነቡ አደረገ። እንዲሁም ካይሮ ውስጥ ያስገነባውን ዓይነት የአዕምሮ በሽተኞች የሚታከሙበት ሆስፒታል ሠራ። የ "ሱብሑ አል-ዓሻ" ደራሲ እንዲህ ይላል፦

> ሱልጣኑ ግብፅን የተቆጣጠረ ጊዜ እ.ሐ.አ በ384 በአል-ዓዚዝ ኢብን አል-መዓዝ የተሠራ ትልቅ አዳራሽ የነበረበትን ቦታ ወስዶ የአዕምሮ በሽተኞች የሚታከሙበት ማዕከል እንዲሆን አደረገው። የውጭ አገር ሰዎች እና እንግዶች ወደ ከተማዋ ሲመጡ የሚያርፉበት በጣም ግዙፍ ህንፃ አስገነባ። በተጨማሪም የገበሬዎችን ሁኔታ የሚያሻሽሉ ድልድዮችን እና የመስኖ ቦዮችን ለመሥራት እቅድ ነበረው።

## የትምህርት ተሐድሶ

ሰላሑዲን ለዕውቀት ትልቅ ፍቅር እና ክብር ነበረው። ምሁራንን ይደግፍና ያበረታታ ነበር። የሀገሪቱ የባህል እድገት እንዲያቆጠቁጥ ለማድረግ ተገቢውን ጥረት አለማድረጉ ወይም በቂ ትኩረት አለመስጠቱ ያሳስበው ስለነበር፣ በርካታ ትምህርት ቤቶችን አስገነባ፣ ዑለፊዎችን፣ ገጣሚዎችን፣ ምሁራንን እና በተለያዩ የባህል ዘርፎች ላይ ባላቸው ጥልቅ ዕውቀት አንቱ የተባሉ ጠቢባንን አመጣ። ቢሒደት "ኩትታብ" በመባል የሚታወቁ ማዕከሎች ተፈጠሩ። ህፃናት በለጋ ዕድሜያቸው ወደ እነዚህ ማዕከሎች (ኩትታቦች) እንዲገቡ ይደረግና ቁርአን እና ሐዲስ

እንዲማሩ፣ የአረብኛ ፊደላትን ውብ አድርገው መሳል እንዲለማመዱ፣ በተጨማሪም ሒሳብ እንዲያጠኑ፣ ግዮሞችን እና የአረብኛ አባባሎችን ወይም ጥቅሶችን በቃላቸው እንዲይዙ፣ እንዲሁም የጀመዓ ሶላት አሰጋገድና የዱዓ ስነ-ሥርአት እንዲያውቁ ይደረግ ነበር።

አንድ ልጅ አድጎ ወጣት በሚሆንበት ጊዜ በትምህርቱ መማሩት ከፈለገ ግብፅ፣ ሶሪያ፣ ሞሱል፣ ባግዳድ ወይም መካ ውስጥ ወደሚገኙ ትላልቅ ማዕከሎች ይሔድ ነበር። ወደ እነዚህ ማዕከሎች የሚገቡ ወጣቶች ድሮ የነበሩ እና አዲስ የተፈጠሩ የተለያዩ የሳይንስ ዘርፎችን ያጠኑ ነበር በመስጂዶች እና በትምህርት ቤቶች በዋናነት ይሰጡ ከነበሩ የትምህርት ዘርፎች ውስጥ አንዱ የነበረውን ቁርአንን በተለያዩ መንገዶች የማንበብ ስልት ይማሩ ነበር። እንዲሁም በተለያዩ የቁርአን ሊቃውንት እና በተለያዩ መንገዶች ይሰጥ የነበረውን ቁርአንን የመተርጎም ጥበብ ይማሩ ነበር።

በሰላሐዲን ዘመን ለነበረው የባህል እንቅስቃሴ መስጅዶች ትልቅ ሚና ነበራቸው። ሶላት ለመስገድ እና ዕውቀት ለመሸመት በሚመጡ ሰዎች ይጨናነቁ ነበር። ብዙ ሰዎች በተለያዩ የሳይንስ ዘርፎችን ለምሳሌ፦ ቁርአንን በማንበብ ስልት፣ ቁርአንን በመተርጎም ጥበብ፣ በሰዋሰው፣ በቃላት አርቢ እና ግንባታ፣ በሥነ-ዕዙፍ፣ በግዮም ወዘተ በየመስጅዶቹ የሚሰጡ ትምህርቶችን በመከታተል በመረጡት መስክ የበቁ ሁነው ይወጡ ነበር።

ካይሮ ውስጥ አምር ኢብን አል-ዓስ፣ አል-አዝሃር፣ አል-አቅመር፣ አል-ሐኪም ቢአምሪላህ እና አል-ሑሴን መስጅዶች እጅግ የታወቁ ነበሩ። አሌክሳንድሪያ ውስጥ የነበረው አል-አሣሪን መስጅድ ደግሞ የኢስላምን ባህል እና ሌሎች ሳይንሶችን በማስፋፋት በኩል ትልቅ ሚና የተጫወተ መስጅድ ነበር። በመላዋ ግብፅ መስጅዶች ተረፈ-ተውና በህዝቡ ውስጥ ዕውቀት ጎልብቶ ነበር።

መስጅዶች ሶሪያ ውስጥም ተመሳሳይ ሚና ነበራቸው። ኢብን ጁበይር ደማስቆን በጎበኘበት ጊዜ የተማረከለትን መስጅድ የሚያህል ግን የሚወዳደረው አልነበረም። የደማስቆ ከተማ በዘመኑ የነበሩ ምሁራን ከመላው ዓለም ተጠራርተው የተሰባሰቡባት የምትመስል የዕውቀት

ማዕከል ነበረች። በጣም ብዙ ተማሪዎችን በመቀበል የሚታወቀው ዳሩል-ሒክማ (የጥበብ ቤት) ትሪፖሊ ውስጥ ይገኝ ነበር። ከግብፁ አቻው (ዳሩል-ሒክማ) ጋር በመተባበር የባህል እንቅስቃሴው እንዲያብብ አድርገውት ነበር።

እ.ሐ.አ በ583 እየሩሳሌም ነፃ ከወጣች በኋላ የተቋቋሙትን ትምህርት ቤቶች ጨምሮ ግብፅ እና ሶሪያ ውስጥ የነበሩ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች አሪፉንም መገዛታቸው በጣም በሰፊው እና በጥልቀት ያስተምሩ ነበር። ሰላሑዲን የመጀመሪያው አስ-ሲዩፊያህ ትምህርት ቤት ገነባ። አስ-ሲዩፊያህ የሐነፊን መዝሃብ ብቻ ለማስተማር የተቋቋመ ትምህርት ቤት ነበር። ሰላሳ ሁለት ሱቆችን ከሠራ በኋላ ገቢያቸው ለዚህ ትምህርት ቤት መደጎሚያ እንዲሆን አበርክቶም ነበር። ይህ ትምህርት ቤት ሌት ከቀን በማስተማር ያለማቋረጥ ምሁራንን ያፈራ ነበር።

እንዲሁም የሻፊኢያህ መዝሃብ ብቻ የሚሰጥበት አስ-ሳለሒያህ የሚባል ትምህርት ቤት ገንብቶ ነበር። እሱ ራሱ የዚህ መዝሃብ ተከታይ ስለነበር ራሱ ኃላፊነቱን ወስዶ ግዙፍ እና ሠፊ እንዲሆን ትልቅ ጥረት ያደርግ ነበር። ከጎኑ የገላ መታጠቢያ ቤቶችን፣ ከፊት ለፊቱ የማብሰያ ቤት እና ምድጃ እንዲሁም ብዙ ሱቆችን ገንብቶ ለትምህርት ቤቱ አበርክቶ ነበር። በተጨማሪም ጀዚራህ አል-ፊል የተባለችውን ደሴት ለዚህ ት/ቤት ሰጥቶ ነበር። አል-መቅሪዚ "አል-ኹታት" በተሰኘው መዕሃፉ ውስጥ እንዳስቀመጠው ይህች ደሴት ከካይሮ ወጣ ብላ በናይል ወንዝ ላይ ትገኝ ነበር።

ሰላሑዲን እ.ሐ.አ በ583 ከተማዋን ነፃ ካወጣ በኋላ የእየሩሳሌምን ትምህርት ቤት ገንብቶ አል-ቃዲ በሐኡዲን ኢብን አል-ሸዳድን እዚህ ትምህርት ቤት እንዲያስተምር አስቀምጦት ነበር። በዘመኑ እጅግ ገዝኛ ባንበረው በኢብን አል-ሸዳድ ለመማር በጣም ብዙ ተማሪዎች ወደ እየሩሳሌም ይተሙ ነበር።

የተለያዩ ኃይማኖታዊና ሳይንሳዊ የትምህርት ዓይነቶች በሚሰጡባቸው፣ እሱ ባቋቋማቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓቱ የተለየ መልክ እንዲኖረው ጥበት ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር። በሰላሑዲን

የተቀረፀው አዲሱ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሚከተለው ነበር። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን ሁለት ምድብ ነበራቸው። የመጀመሪያው ምድብ በሚሰጡት የትምህርት አይነት በጣም ጥልቅ ዕውቀት የነበራቸውን እና በብቃታቸው የተመሰከረላቸውን መምህራን የሚይዝ ሲሆን፤ ሁለተኛው ምድብ ደግሞ በመጀመሪያው ምድብ የተሰጡ ትምህርቶችን ደግመው የሚያስተምሩ እና በደረጃቸው ከመጀመሪያው ምድብ ዝቅ ያሉ መምህራንን የያዘ ምድብ ነበር። የሁለተኛው ምድብ መምህራን ዓላማ፤ በመጀመሪያ ደረጃ በመምህራን የተሰጡ ትምህርቶችን ደግመው በማስተማር፤ ተማሪዎች በትክክል እንዲረዷቸው መርዳት እና ደካማ ተማሪዎችን ረጅም ጊዜ ወስደው በማስረዳት ተማሪዎቹ ማወቅ የሚጠበቅባቸውን ዕውቀት እንዲጨብጡ ማገዝ ነበር። ከሁለተኛው ምድብ ውስጥ የሚገኝ መምህር የአንደኛው ምድብ መምህር ክፍል ውስጥ በሚያስተምርበት ጊዜ በተዘጋጀለት ልዩ ቦታ ላይ ተቀምጦ እስከመጨረሻው ድረስ ትምህርቱን ሲከታተል ከቆየ በኋላ የአንደኛው ምድብ መምህር ጨርሶ ሲወጣ በእሱ ቦታ ተተክቶ ያንኑ ትምህርት ደግሞ እንዲያስተምር ይደረግ ነበር። ጥያቄዎቻቸውን በመመለስ ወይም እንዲብራሩላቸው የሚፈልጓቸውን ነጥቦች በማብራራት ወዘተ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንዲረዱት የማድረግ ኃላፊነት ነበረበት። ይህ የማስተማር ዘዴ በዘመናችን በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ፕሮፌሰሮች ካስተማሩ በኋላ ሌክቸሮች ተተክተው ትምህርቱን እንዲቋጩ ከሚደረገው ሥርዓት ጋር ያለጥርጥር ይመሳሰላል።

በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ይጠኑ የነበሩት የትምህርት ዓይነቶች የነረዲንን ህልም በተግባር የሚተረጉመ፤ የሰናን መንገድ ዳግም መመለስን እና ማስፋፋትን ያለመ እንደነበሩ ግልፅ ነው። ፋጢሚዮች የተከሳቸውን የተሳሳቱ እምነቶች እና አስተሳሰቦች ከሥራቸው መንግሎ ማጥፋት እና አገሩን በሙሉ የበከሉትን ፍራንኮችን ህገ-ወጥ እንዲታገላቸው ማበቃት ነበር ህልመ።

ያን ጊዜ የመጽሐፍት ገበያ የጦፈ እና የነቃ ነበር። ግብፅ ውስጥ በጣም ድንቅ እና ትልቅ ዋጋ የነበራቸው መጽሐፍት የሚሸጡባቸው ብዙ የመሸጫ ቦታዎች ነበሩ። በተለይ ከአምር ኢብን አል-ዓስ መስጅድ

በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በጣም የታወቀና የመጽሐፍት ገበያው የደራበት ቦታ ነበር። ደማስቆ ውስጥም እንዲሁ በዓይነት ተቆጥረው የማይዘለቁ መፅሃፍትን ያካተተ የመጽሐፍት ብዛ የሚቀርብበት ግዙፍ የሆነ የመጽሐፍ ገበያ ነበር።

## ኢኮኖሚያዊ ሀዳሴ

የሰላሐዲን ዘመን፣ የህዝቡ ሕይወት የእውነት የተለወጠበትና ህዝቡ በሃብት የተጥለቀለቀበት ዘመን ነበር። ሠፊ ግዛቱ በበርካታ ተፈጥሯዊ ሃብቶች የከበረ ነበርና ይህ ቢሆን የሚገርም አይሆንም።

በተጨማሪም በርካታ የሐብት ምንጮች ነበሩት። የሚከተሉትን ዋና ዋና ምንጮች መጥቀስ ይቻላል፦

1. ግብፅን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ መምራት ሲጀምር የተረከባቸው የፋጢሚዮች ካዝናዎች
2. ሙስሊም ካልሆኑ ዜጎች የሰበሰበው ጂዚያ (የግብር ዓይነት)
3. ከመስቀል ወራሪ ምርኮኞች የሰበሰበው የቅጣት ገንዘብ ወይም እራሳቸውን ከምርኮኝነት ነፃ ያወጡበት ክፍያ
4. ከጦርነቶች ያገኘው ምርኮ (ሐብት)
5. ሙስሊሞች ያለጦርነት ከያዟቸው ወይም በስምምነት ከተቆጣጠሯቸው ክልሎች ያገኘ የነበረው የመሬት ግብር።

ሰላሐዲን የነበረውን ሐብት እጅግ ጠቃሚ ለሆኑ ፕሮጀክቶች ያውለው ነበር። ለምሳሌ ለጅሃድ፣ የመከላከያ ኃይሉን ለመገንባት፣ ባህልን እና እውቀትን ለማጎልበት፣ የህዝቡን ኑሮ የሚያሳድጉ ግንባታዎችን ለመከወን እና ሌሎች ጠቃሚ አገልግሎቶችን ለማሟላት ይጠቀምበት ነበር። ከዚህም በላይ አጠቃላይ ኢኮኖሚውን የሚያሳድጉ ተግባራትን ያከናውን ነበር።

የተራዘመው ጦርነት የወለዳቸውን የተለያዩ ችግሮች ለመቅረፍ ዘርፈ ብዙ እርምጃዎችን ይወስድ ነበር። ለምሳሌ ርሃብን ለማስወገድ፣ ለግብርና ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ነበር፣ ሁሉንም የአትክልት እና

የፍራፍሬ ዓይነቶች ማምረት እንዲቻል የመስኖ እርሻዎች ላይ በሠፊው ይሠራ ነበር። ግብፅ እና ሶሪያ የግብርና ውጤቶችን በመለዋወጥ፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስራቸውን በማሳደግ እና የሠራዊቶቻቸውን ፍላጎቶች በማሟላት ይተባበሩ ነበር። እንዲሁም የጋራ ጠላቶቻቸውን በጋራ በመከላከል እና የመስቀል ወራሪዎችን ለሚታገሉ ሙስሊም ወታደሮች አስፈላጊውን ስንቅ እና ትጥቅ በማቅረብ ለጋራ ዓላማ በጋራ ይሠሩ ነበር።

ለንግድም እንዲሁ ትልቅ ፍላጎት ነበረው፣ ግብፅ የምስራቁና የምዕራብ ዓለም የሚገናኝባት የንግድ ማዕከል እንድትሆን ተግቶ ይሠራ ነበር። በዚህ የንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት ብዙ የአውሮፓ ከተማዎች አድገዋል። ለምሳሌ ቬኒይስ (Venice) እና ፒሳ (Pisa) የንግዱ ትሩፋት ተጠቃሚ ከነበሩና ከፍተኛ እድገት ካሳዩ አውሮፓዊ ከተማዎች ውስጥ የሚጠቀሱ የጣሊያን ከተማዎች ነበሩ። ቬኒቲያኖች አሌክሳንደሪያ ውስጥ "አል-አይክ" ተብሎ የሚጠራ ትልቅ የንግድ ቦታ መሥርተው ነበር።

ግብፅ እና ሶሪያ ውስጥ የሚገኙ የንግድ ቦታዎችን በማሻሻል፣ በማስፋፋት እና አዳዲስ የንግድ ማዕከሎችን በመገንባት የንግድ እንቅስቃሴውን ይደግፍ ነበር። በመሆኑም ኢኮኖሚው ሊያድግ እና ምርቱም ሊጨምር ችሏል። ተንዡ ኢብን ጅበይር አ.ሐ.አ በ578 ወደ እነዚህ የገበያ ማዕከሎች ሲደ የተመሰኑ ቦታዎችን ከሳበኝ በኋላ አድናቆቱን ገልፆ ነበር። ስለ አሌፖ የሚከተለውን ፅፏል፦

> ውብ እና ድንቅ ከተማ ናት። ገበያዎቿ በጣም ትላልቅ፣ በጣም ሰፋፊ እና እርስ በርስ በሥርዓት የተያያዙ ናቸው። የተለያዩ ምርቶች እና ቁሳቁሶች በገፍ ይገኛሉ። እያንዳንዱ ምርት ወይም ቁስ በገበያው ውስጥ የሚገኝበት የራሱ የሆነ ወይም የተለየ ቦታ አለው። ሁሉም የገበያ ቦታዎች ነዋሪዎቿ የሚጠለሉባቸው ከእንጨት የተሰሩ ጣሪያዎች አሏቸው። ሁሉም ቦታዎች ዓይን ይይዛሉ፣ የቸኮለን ሰው አናዝዘው ያስቀራሉ። ሁሉም ያየኋቸው ሱቆች በሚያምሩ የእንጨት [illegible] የተሠሩ ናቸው።